# *ሻዕብያን መውጋት ወይስ መቅበር?*

*ከብስራት ከበደ*

በተለያዩ ግዜያት ልማታችንና እድገታችን ስኬታማ እንዳይሆን የሻዕብያ መንግስት አፍንጫችን ስር ሆኖ አገራችን ኢትዮጵያን ለማተራመስ ከፀረ-ሰላም ሃይሎች ጋር ግንባር በመፍጠር ብሎም ዓለም አቀፍ ሽብርተኞችን በማሰባሰብ ሌት-ቀን እሳትና ረመጥ የሚለኩስብን ሃይል የኢትዮጵያ መንግስት ቀደም ብሎ በሻዕብያ መንግስት ላይ ወታደራዊ እርምጃ ለምን አልወሰደም? ሰሞኑን በእስላማዊ ፍ/ቤቶች ህብረት ላይ የተወሰደው ወታደራዊ እርምጃ ተከትሎስ በሻዕብያ ላይ እርምጃ የማይወሰድበት ምክንያት ለምንድነው በሚል ርእስ በአይጋ ድረ-ገጽ ላይ ከቀረበው አስተያየት ተንደርድረን እስቲ የሚከተሉትን ሃሳቦች አብረን እንያቸው!!

1. የኢትዮጵያ መንግስት አቋም በቅድሚያ የመጀመርያው ጠላት (ድህነት) መዋጋት መሆኑ ሁላችንም የምንገነዘበው ሃቅ ነው። ከዚሁ ሃቅ ጋር የማትጋሩ ወገኖች ግን ይቅርታችሁን እጠይቃለሁ። ታድያ የመጀመርያው ጠላት ሻዕብያ ነው። ምክንያቱም ድህነት ለመዋጋት ስንዘጋጅ ሰላማችን በማደፍረስ ለልማታችንና ለዕድገታችን ጠንቅ በመሆን ድህነት እንዳንዋጋ እንቅፋት እየሆነብን ስለሆነ የመጀመርያው ጠላታችን ሻዕብያ አይደል? የምትሉኝ ከሆነ ካሁን በፊት ከሻዕብያ ጋር የተካሄደው ፍትሃዊ ጦርነት መለስ ብለን ማጤን የግድ ይሆናል። ያኔ ኀረምሳው ሻዕብያ ጦሩን ሰብቆ ታንኮቹን አሰልፎ ባድሜንና አከባቢውን ሲወር፣ ፊትለፊቱ ያገኘውን ሰው ሆነ እንስሳ ጨፍልቆ፣ በትምህርትና በህክምና ተቋሞች ላይ ግዜያዊ ምሽግ ሲቆፍር፣ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ለግዜው የተወሰደው አቋም፣ "በእብሪትና በሃይል ከያዝከው መሬት ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ውጣልን" የሚል ብቻ ነበር። የምታስታውሱት ከሆነ በኢትዮጵያ በኩል "እያንዳንዱ የሰላም ቀን እኛ ተጠቃሚዎች ነን" በሚል መርህ መንግስት አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ የሰላም አማራጮች ተሟጠው ካለቁ በኃላ ነበር ተገዶ ወደ ጦርነት የገባው። በወቅቱ ትናንት የሰሜኑ የአገራችን ክ/ሃገር የነበረችው ሚጢጢ ኤርትራ እንዴት ኢትዮጵያን የሚያክል አገር አምበረከከች በሚል ሃዘን ልቡ ያልተነካ ኢትዮጵያዊ ነበር

ብዮ አላምንም። የኢህአዲግ መንግስትም ያላሰበውና ያላብሰለሰለው ዱብ ዕዳ እንዳጋጠመው ማንም የሚተረጉመው ክስተት ነበር። ይሁንና ለቀዳሚው ጠላት (ድህነት) ለመውጋት ሲባል እግዚአ፣ ከመሬታችን ውጣልን የሚል አቋም ተያዘ። ይህ የውጣልን እግዚአ ዘጠኝ ወራት ያስቆጠረ ልመና ከመሆኑም ባሻገር አሜሪካም ሩዋንዳም እንዲሆም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት) ያሳተፈና እልህ አስጨራሽ ልመና ሆኖ እንደከረመ ግልፅ ነው። ያም ሆነ ይህ አጉል ፈሊጡ የሻዕብያው መሪ አቶ ኢሳያስ አንዴ በፀሃይ ግባት አንዴም በጨረቃ መውጣት ሲምሉ፣ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት የመጀመርያው ጠላት ድህነት ለማስወገድ ደፋ-ቀና በሚልበት ወቅት ከደርግ ውድቀት ማግስት ጀምሮ ውግያ የረሳ መስሎ ይታይ እንደነበር ሳትገነዘቡት ያለፋችሁ አይመስለኝም። ይሁንና በወቅቱ ሌላ አማራጭ በመጥፋቱ የግድ ሆነና ወደ ጦርነት ተገባ። በመሆኑም ዘመቻ ፀሃይ ግባት የሻዕብያ ምሽግ ድረስ ዘልቆ አንኳኳቸው። ያ የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ እስከ ባሬንቱና ተሰነይ አሳደዳቸው። በወቅቱም የሻዕብያ መሪ አቶ ኢሳያስ በሬድዮ እንደገለፁት ሽንፈታቸውን ላለማመን በጣም ጥሩ ትምህርት አግኝተናል ሲሉ ከሞት የተረፈው ሰራዊታቸው ሽሽት ነበር የያዘው።

ወደ ቁምነገሩ ልመልሳችሁና፡ ታድያ ለምን "ባይደዋና ኪስማዮ" ተዘልቆ "ሞቃድሾ" እንደተገባና የእስላማዊ ፍ/ቤቶች ኅብረት እስከ ኬንያ ማሳደድ እንደተያዘ ሁሉ፣ ባሬንቱና ተሰነይ ተገብቶ ሻዕብያን እስከ ቀይ ባህርና ከሰላ ድረስ ማሳደድ አልተቻለም የሚል ጥያቄ በብዙዎቻችን ጭንቅላት የሚብሰለሰል እውነታ መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም። በፈረንጆች ሁለት ሺህ ዓ/ም ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ዋሽንግተን ዲሲ መጥተው ከአንድ አስተያየት ሰጪ "አስመራ ድረስ ገብታችሁ ኢሳያስን አለማሳደዳችሁ አሜሪካ ምን ያህል ቢጫጫናችሁ ነው"? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው እንደነበር የቅርብ ግዜ ትውስታችን ነው። ሆኖም ከግዜ ወደ ግዜ ግልፅ እየሆነ የታየው ነገር ቢኖር ጉዳዩ ሚዛናዊ አስተሳሳብ (Critical Thinking) የሚጠይቅ መሆኑ ነው። በዛን ግዜ የኢትዮጵያ መንግስት ሻዕብያን ከምድረ-ገፅ የማጥፋት ሃይሉ ነበረው ተብሎ ቢታመንም በዓለሙ ማ/ሰብ በተለይም በአሜሪካ መንግስት ዘንድስ ተቀባይነት ነበረው ወይ ብሎ ማሰብ ጠቃሚ ይመስለኛል።

እንዲህ ስል ግን የኢትዮጵያ ልዓላዊነት በተደፈረ ቁጥር የመልሶ ማጥቃት እርምጃው ያለ የአሜሪክ መንግስት ፍቃድ መተግበር የለበትም ማለቴ ሳይሆን የዓለሙ ማ/ሰብ ድጋፍ ያስፈልጋል ማለቴ እንደሆነ ተረዱልኝ። የምታስታውሱት ከሆነ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ወደ ውጭ እንዳይወጡ እስከ መከልከል ድረስ በአቶ ክሊንተን እርምጃ ለመውሰድ በዝግጅት ላይ እያሉ እኮ ነው መከላከያ ሰራዊታችን ከኤርትራ መሬት እንዲወጣ የታዘዘው። በዛ ሁኔታስ እንዴት ሆኖ ነው ሻዕብያን እስከ ከሰላና ቀይ ባህር ማሳደድ የሚቻለው? ከእስላማዊ ፍ/ቤቶች ህብረት ጋር የተካሄድው ጦርነት ግን የአሜሪካ የጦር አውሮፕላኖች ሳይቀሩ እኮ ነው በጦርነቱ ተሳትፈው ድጋፋቸው የገለፁት። እስቲ ልዩነቱን እዩት፣ በOk እና በNo መካከል ያለው ልዩነት ነው። ስለሆነም በኔ አስተያየት በዛ ምክንያት ይመስለኛል እንግዲህ ሻዕብያ ያኔ ሊጠራረግ ያልቻለውና የዛሬ ራስ ምታት ሆኖ የተቀመጠው። ይሁንና የሻዕብያ መንግስት ለዘጠኝ ወራት ያህል ተልምኖ የኢ/ያ ህዝብ ጦርነት ላይ ተገዶ በመግባቱ የተከፈለው መስዋእትነት ግምት ውስጥ በማስገባት መሬት ላይ የወደቀውን ሻዕብያ አስነስቶ በአልጀርሱ ድርድር እንዲቀርብ ማድረግ ሻዕብያን ማስታመም ሆኖ ስለታየኝ እስከዛሬ ድረስ ድራማው ሊገባኝ ባይችልም ምናልባት ለሰላምና ለተኩስ አቁም ሲባል በሰጥቶ መቀበል ጉዳይ ላይ ያተኮረ ሊሆን ስለሚችል የአልጀርሱ ነገር የሚመልከተው አካል ማብራሪያ እንዲሰጥበት ትቸው ባልፍ ይሻላል።

2. ሽብርተኝነት ለአሜሪካ ህዝብና መንግስት ምን ያህል እንዳስደነገጠው የአደባባይ ሚስጥር ነው። በዚሁ ሳብያ በሃዋይ ስቴትም ሽብርተኞች ካሉ ህጄ ልውጋቸው የሚል መንግስትም ሆነ ድርጅት በዚህ ዓለም ቢኖር የአሜሪካ መንግስት የማይለግሰው ሞራልና ማቴርያል እንደማይኖር ሳይታለም የተፈታ ነው። ስለሆነም በሶማሊያ የመሸጉ የአልቓይዳ ቅሪተ አካሎች አሉና እኔንም እያስፈራሩ እናንተንም ቀናችሁ ጠብቁ እያሉዋችሁ ነው የሚል ዜና አሜሪካኖች ሲሰሙ፣ እንዳውም ግዜ አትስጡዋቸው የሚል ምላሽ እንደሚሆን ግልፅ ነው። ቅድም እንደጠቀስኩት አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል ምንግዜም ከአሜሪካን መንግስት ፍቃድ መጠየቅ አለባት ማለቴ አይደለም። ይልቁንስ ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል የዓለሙ ማ/ሰብ ድጋፍ

በጣም አስፈላጊ ነው ለማለት ፈልጌ እንደሆነ ትረዱልኛላችሁ የሚል እምነት አለኝ። ስለዚህ እነ ጣሂር ሃዌሶች ጨረቃም ቢጓዙ አሜሪካ ተከታትላችሁ አጥፉዋቸው እንደምትል የሚያጠራጥር አይሆንም። በዚሁ አጋጣሚ ከእስላማዊ ፍ/ቤቶች ጋር ተሰልፎ ሻዕባያ የጦር መሳርያ፣ የወታደር የሎጂስቲክ ድጋፍ በመስጠት እኛን ለማጥቃት ስለተነኮሰን በመረብ በኩል ዘልቀን እናጥፋው የሚል ጥያቄ ለዓለሙ ማ/ሰብ ቢቀርብ የሚገኘው መልስ ምን መሆን እንደሚችል መተምበይ ከባድ ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ በመዳከምና በመፈራረስ ላይ ያለው ሰራዊት ጋር ሄዶ መስዋእት መክፈል አስፈላጊ ነው ወይ? ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን ዛሬም እንደትናንቱ ከሻዕብያ ጋር የሚያካሂደው የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ በአጭር ግዜና በድል አድራጊነት እንደሚወጣ የሚያጠራጥር ባይሆንም እየሞተ ያለውን ሃይል ለመግደል መስዋእት አስፈላጊ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ሚዛናዊ ብይን ነው። ስለዚህ በኔ እምነት ክሳድ ዒቃና ዓይላ ጉንደት ተሻግሮ ጦርነት በማወጅ ልዑላዊነታችን እስካልደፈረ ድረስ አንድም ወታደር ለመስዋእት ማቅረብ ተገቢ አይመስለኝም። ሌላው ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ፣ ሻዕብያ በኢረ ቲቪ የሚያናፍሰው አፍራሽ ፕሮፖጋንዳና ነጭ ውሸት ለመግታት ከውጭም ሆነ ከሃገር ቤት ምሁራንና በሞያው የተካኑ ዜጎች በማሳተፍ የሻዕብያ ፕሮፖጋንዳ ማፍሸል ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት ይገባል።

ሻዕብያን እንደ አክራሪው የእስላማዊ ህብረት መጥረግ ቢቻል እንኳ በኤርትራ ውስጥ የተቀናጀና የተደራጀ የሽግግር መንግስት ከሌለ አገሪቷ ተርክቦ የሚያስተዳድር አካል እንደሚያስፈልግ ግልፅ ነው። ከአሁን ቀደም እንደታየው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እንደሆነ ሻዕብያን ከጠራረገ በኋላ እኮ በተወሰነ ግዜ መውጣት ስለሚኖርበት ዞሮ ዞሮ ኤርትራ የሽብርተኞች መናሃሪያ ከመሆን አታልፍም የሚል ስጋት መኖሩ ግልፅ ነው። በሌላው በኩል በተለያዩ ሚድያዎች እንደተገለፀው የኤርትራ ህዝብ 60% ሙስሊም ነው ይባላል። ስለዚህ ኢሳያስ የኤርትራን ህዝብ እያሰቃየ ቢገዛም በዛ አከባቢ የባሰ ብጥብጥና አለመረጋጋት እንዳይከሰት በምእራባውያን ዘንድ ኢሳያስ እንደ ትልቅ መሳርያ እንደሚያገለግል

ይነገራል። ስለሆነም በኤርትራ ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ መንግስት ማቋቋም መብቱና ግዴታው የኤርትራ ህዝብ ጉዳይ ስለሆነ በዲክተር ኢሳያስ አፈወርቅ ላይ የትጥቅም ሆነ የሰላማዊ ትግል የሚያካሂዱ ድርጅቶችን ማገዝና ማጠናከር እንደ አማራጭ መወሰድ ያለበት ጉዳይና የቀለለ መንገድ ይመስለኛል።

በሌላው በኩል፡ እኛ ኢትዮጵያውያኖች ዋናው ጠላታችን ድህነት ነው ብለን ካስቀመጥን፡ በድህነት ዙርያ የሚካሄደው ውግያና ትግል ማሰብ እንጂ ከዕብድ ጋር ማበድ ትክክለኛ አይመስለኝም። ከአሁን በፊት በኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት እንደተገለጸው፣ "ሻዕብያ ሳንዋጋ እንዳይዋጋ ሽባ አድርገነዋል" ብሏል። ስለዚህ ሁላችንም እንደምንታዘበው ሻዕብያ በቁሙ እየሞተ እንደሆነ ክሳድ ዒቃንና መረብን ተሻግሮ መዋጋት ሲገባው በአስር ሺዎች ኪሎ-ሜትር ተጉዞ በመቃዲሾ በኩል በእጅ አዙር ሽብር ለመፍጠር መሞኮሩ ምን ያህል ሽባና ዓቅመ ደካማ መሆኑ አመላካች ነው። ከዚህ ጎን ለጎን አገራችን ኢትዮጵያ በሰዓታትና በቀናት ውስጥ በኢኮኖሚውና በቴክኖሎጂው ዕድገት በፍጥነት እየተጓዘች ባለችበት ግዜ ከማይረባ ሽማግሌ ውሻ ጋር መጯጯህ ለአገራችን ህዝቦች ምንም የሚሰጠው ፍሬ ሊኖር አይችልም። ከሽባ ጋር እልህ ተያይዞ ኃላ መቅረት ከሻዕብያ በላይ እኛን የሚጎዳ ሁኔታ እንደሚሆን ከወዲሁ የሚገመት ጉዳይ እንጂ እናንተን መስበኬ አይደለም።

በአጠቃላይ ሲገመት ሽብርተኝነት የዓለማችን ህዝቦች የሚሰጉበት ክስተት እንደሆነ እየተዋለም ሆነ እየታደረ የሚስተዋል ጉዳይ ስለሆነ የመስከረም 11 ጥቃት በዒራቅ፣ በአፍጋኒስታንና በሌሎች አገሮች ወታደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ አብይ ምክንያት እንደሆነ የተለያዩ ምንጮች እየጠቆሙ ነው። ምናልባትም በአቶ ሳዳም ሁሴን የተወሰደው ዘግናኝ እርምጃም ዋናው ምክንያት የመስከረሙ ጥቃት እንደሆነ የብዙ ዜጎች ግምት ነው። የመስከረም 11 እልቂት ባይከሰት ኖሮ አሜሪካ በሳዳም ሁሴንና በዒራቕ የወሰደችው ወታደራዊ እርምጃና የፍርድ ሂደት አትወሰድም ነበር የሚሉም ወገኖች ብዙ ናቸው። ሻዕብያም ሆነ ሌላ ድርጅት በሽብር ተግባር ላይ እስከተሳተፈ ድረስ ይሰነብታል ማለት ዘበት ነው። ምናልባት የሻዕብያ መጥፋት ትልቁ መንስኤ የሚሆነው አሜሪካ፣ አውሮጳ ወይንም ኢትዮጵያ ሳይሆኑ ራሱ ሻዕብያ ነው። በትግርኛ አንድ አባባል አለ። "እነ'ዶ ከይሕዛ እዛ ነዊት፣ ንስኺ'ዶ ከይትበልዒ ሸዊት፣

ተታሒዝና መስከረም ንመውት"። ትርጉሙ፡ እኔ እንደሆንኩኝ መፎር አልይዝ፣ አንቺም እሸት አትበይ፣ ተያይዘን መስከረም እንሞታለን ነው። ስለዚህ ሻዕብያ እንደሆነ ታሟል፣ ስለታመመም እጁ በሽብር ተግባር እየነከረ እንደሆነ ግልፅ ነው፣ በመጨረሻም እንደ ሳዳም ማነቆ ውስጥ ሳይገባ እንደማይቀር በመጠኑ መገመት አያዳግትም። እስካሁን ግዜ ድረስ አሜሪካንና የአውሮጳ አገሮችም በኢሳያስ ላይ እርምጃ ያልወሰዱበት ምክንያት የታመመና ራሱን የጣለ መሪ ቢጮህም ቢሳደብም ብዙ የሚያሰጋ ስለማይሆን ብዙ አገሮች ጆሮ ዳባ ልበስ እያሉት መሆኑ ይስተዋላል። ያም ሆኖ ለሁሉም ልክ አለውና ሻዕብያ ከመሳደብና ከመጮህ አልፎ በሽብር ተግባር ላይ የመሳተፉ ጉዳይ ከቀጠለ አቶ ሳዳም ሁሴን ያጋጠማቸው ፍርድ እንደሚያጋጥመው በሂደት የምንገነዘበው ጉዳይ ይሆናል። ስለዚህ የሻዕብያ ጉዳይ ለውይይትና ለክርክር መቅረብ ያለበት ጉዳይ ቢሆንም ሻዕብያ አንዴ በጦርነት አለያም ደግሞ በሽብርተኝነት እየተሳተፈ ገደል አፋፍ ላይ ስለሚገኝ ገበሬ ካላመረተ በርሃብ እንደሚሞት ሁሉ ኢሳያስም ለሰላምና ለዕድገት እጁን እስካልዘረጋ ድረስ ራሱን እስኪቀብር ብቻ መጠበቅ እንጂ ከሽባ ጋር ግዜ ማባከን አስፈላጊ ሆኖ አይታየኝም።

አስተያየታችሁ አፅናኝ፣ አዝናኝ፣ ትምህርት ሰጪና አበራታች ስለሆነ ፃፉልኝ። በዚሁ አጋጣሚ ባለፈው ሳምንት "የሽብርተኞች ቡድን ምን ያህል ተጠርጓል?" በሚል ርእስ በፃፍኩት ፅሁፍ ላይ ለላካችሁልኝ ገንቢ ሃሳብ ልባዊ ምስጋናዮን አቀርባለሁ።

besrattshore@yahoo.com

መልካም ሳምንት!!